# ደምብ-ሥርዓት

MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ

**ተዛማጅነት ያላቸው ግብአቶች፡-** ACA፣ ACF፣ ACF-RA፣ ACH፣ ACH-RA፣ COA፣ COB-RA COC-RA፣ COE-RA፣ COF-RA፣ COG-RA፣ EBA-RA፣ EBJ-RA፣ EBK-RA፣ ECC-RA፣ EEA-RA፣ EKA-RA፣ GKA-RA፣ IGN፣ IGO-RA፣ JFA፣ JFA-RA፣ JGA፣ JGA-RA፣ JGA-RB፣ JGA-RC፣ JGB-RA፣ JHC፣ JHC-RA፣ JHF-A፣ JHG-RA፣ JPD፣ JPD-RB፣ Negotiated Agreements

**ኃላፊነት ያለው ጽ/ቤት፡-** የአካዴሚ/ትምህርት ዋና ኃላፊ
Chief Operating Officer ዋና የሥራ ኃላፊ

## አስፈሪ/አስጊ የሆነ ባህርይን መመርመር

I. **ዓላማ**

ሠላማዊ እና ደህንነቱ የተጠበቀ የትምህርት ቤት ድባብ ለመጠበቅ፣ ተጠቂዎችን ከጥቃት ለመጠበቅ እና ለመከላከል፣ እና ምርመራ እየተደረገ ያለ(ች) ግለሰብን እንደአስፈላጊነቱ ድጋፍ ለመስጠት ተገቢ ለሆነ እርምት እና የመከላከል እርምጃ የሚያበቃ በጥናት ላይ የተመሠረተ ዛቻና ስጋትን የመመርመር ሂደትን መፍጠር

II. **ትርጉም**

A. የዛቻና የስጋት ምርመራማለት የተለያዩ ነገሮችን አጠቃሎ የሚይዝ የሚታይ (ወይም ምክንያታዊ ሆኖ ለማየት የሚያስችል) ባህርዮችን ምን ያህል አደገኛ ሊሆኑ እንደሚችሉ፣ ወይም የረብሻ ሁኔታዎችን፣ በመመርመር እና በማመዛዘን ምላሽ መስጠት ነው።

1. የአስጊ ባህርይን መገምገም ማመዛዘን ማለት በግለሰብ ወይም በቡድን የተነባጠሩ ጥቃቶችን ለይቶ ለማወቅ፣ መመርመር፣ እና ማኔጅ ለማድረግ የሚካሄድ የተዋቀረ የቡድን አሠራር ነው።

2. "የግጭት መንገዶች" በሀሳብ ተጀምሮ ወደ ጥቃት የሚያድግ ባህሪይ እና የታሰበበት ጥቃት የማሰብ የመጨረሻዉ ዉጤት ነዉ በሚል ጽንሰሀሳብ ላይ የተመረኮዘ ምርምርን መሰረት ያደረገ የስጋት ምርመራ/ግምገማ ማለት ነዉ።

3. የማስፈራራት ስጋትን መመርመር ማለት የጥላቻ ወይም የዲስፕሊን ሂደት አይደለም።

B. ዛቻ ወይም ማስፈራራት ማለት የአካል ጉዳት ለማድረስ የዝንባሌ አገላለጽ ነው። ዛቻ/ማስፈራራቱ ምናልባት ሊገለጽ የሚችለው በባህርይ፣ በቃል፣ በምልከታ፣ በጽሑፍ፣ በኤሌክትሮኒክስ፣ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ ሊሆን ይችላል፤ እናም ዒላማ የተደረገበ(ባ)ት ሰው ቢያውቅም ባያውቅም/ብታውቅም -ባታውቅም በቀጥታ ዒላማ በተደረገበ(ባ)ት ሰው ቢስተዋልም ወይም ቢሰነዘርበትም/ቢሰነዘርባትም ወይም በሦስተኛ ወገን ቢታወቅም/ባይታወቅም ወይም ቢሰነዘርም ዛቻና ማስፈራራት-ስጋት ተደርጎ ይቆጠራል። ዛቻ በቀጥታ ማስፈራራት ሊሆን ይችላል (ለምሳሌ፡- "እኔ እመታሃለሁ/እመታሻለሁ።") ወይም በተዘዋዋሪ (ለምሳሌ፡- "አገኘዋለሁ/አገኛታለሁ/ማግኘቴ አይቀርም።")

1. የዛቻው-የማስፈራራቱ አስጊነት ዝቅተኛ ነው የሚባለው የሚዝተው/የምትዝተው ሰው/ሁኔታዉ የምር ጉዳት የማያደርስ/የማታደርስ/ስጋት የማያስከትል ሁኔታ መሆኑ ከታመነ፣ እና ማናቸውም የተከሰቱ ጉዳዮች በቀላሉ የሚፈቱ ከሆነ ነው። አነስተኛ ስጋት የሚባሉ ዛቻዎች/ማስፈራራቶች በትምህርት ቤት አስተዳደር መደበኛ የዲስፐሊን ሥርአት በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የተማሪ ስነምግባር ደምብ መሠረትሊካሄድ ይችላል። የባህሪ ስጋት/ማስፈራራት ግምገማ-ምርመራ ቡድን Behavior Threat Assessment Team (BTAT) (Section III, A and B ይመልከቱ)፣ እንደየአግባቡ፣ ለተማሪው(ዋ) ድጋፍ እንዲሰጥ ሊጠየቅ ይችላል።

2. መለስተኛ ዛቻና ማስፈራራትየሚባለው ሰውየው(ዋ)/ሁኔታው የምር ጉዳት የሚያደርስ-የምታደርስ መስሎ ካልታየ፣ በዚህ ወቅት፣ ነገር ግን ሁኔታው በዚህ አይነት ባህርይ የሚቀጥል አዝማሚያ የሚያሳይ-የምታሳይ ከሆነ እና ለወደፊት ሁከት-ብጥብጥ-ኃይል ወይም አሳሳቢ፣ከባድ፣ከፍ ያለ ጉዳት፣ እና/ወይም ጣልቃ ገብነት የሚያስፈልገው ሌላ አስጊ የሆነ ባህርይ ካሳየ(ች)። መለስተኛ ዛቻ/ማስፈራራትም ቢሆን ተነፃፃሪ የሆነ የትምህርት ቤት ዲስፐሊን ሂደት ይኖረዋል።

3. ከፍተኛ ዛቻ-ማስፈራራት ማለት የሰውየው/የሴትየዋ ሁኔታ ከባድ ጉዳት የሚያደርስ መስሎ ሲታይ፣ ጉዳት የማድረስ ዝንባሌ በተከታታይ ሲያሳይ/ስታሳይ እና ድርጊቱን ለመፈጸም ባለው-ባላት እቅድ የሚያደርጋቸው/የምታደርጋቸው ጥረቶች፣ እና ሌሎችም ጣልቃ ገብነት የሚያሻቸው አስጊ ባህርዮች። በጣም አስጊ ዛቻ/ማስፈራራት ተነጻፃሪ የሆነ የትምህርት ቤት ዲስፐሊን ሂደት ጭምር ያካትታል።

4. አይቀሬ አይነት ዛቻ/ማስፈራራትማለት ሰውየው/ሴትየዋ ግልጽ የሆነ እና ወዲያው የሚሆን አይነት ዛቻ/ማስፈራራት መገታት ያለበት አሳሳቢ ጠብ እና በተለይ ዒላማ የተደረገ(ች)ውን ወይም ተለይቶ የሚታወቅ ዒላማ(ዎች) ላይ ጉዳት እንዳይደርስ የመከላከል እርምጃ እና ሌላም ጣልቃ መገባት ያለበት አስጊ የሆነ ባህርይ። አይቀሬ አይነት ዛቻ/ማስፈራራት ተነጻፃሪ የሆነ የትምህርት ቤት ዲስፐሊን ሂደትን ይጨምራል።

5. ዝምድና/ግንኙነት የሌለው-የሌላት ሰው የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሠራተኛ፣ ተማሪ፣ ኮንትራክተር፣ የቤተሰብ አባል፣ ወይም የተማሪው(ዋ) ጓደኛ ወይም የሥራ ባልደረባ ያልሆነ(ች) ማለት ነው።

C. የአእምሮ ጤንነት አገልግሎቶች አስተባባሪ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የትምህርት ቤት ዲስትሪክት ለማገልግለ በተማሪ እና የቤተሰብ ድጋፍ እና ተሳትፎ ጽ/ቤት (OSFSE) ተከታዮቹ ሃላፊነት ያለበ/ባትን ዲስትሪክት አቀፍ የአእምሮ ጤና አገልግሎት አስተባባሪ ሰይሟል -

1. እየተካሄዱ ያሉትን የአእምሮ ጤና አገልግሎቶች እና ለአእምሮ ጤና አገልግሎት ወደ ሌላ የመምራት/ማስተላለፍ ሂደቶችን ማስተባበር፣

2. ተማሪን ወደ ህክምና ለማስተላለፍ ከሞንትጎመሪ ካውንቲ የጤና እና ሰብአዊ አገልግሎት ዲፓርትመንት (DHHS)፣ እና ሌሎች የአካባቢ የአእምሮ ጤና አገልግሎት ሰጪዎች ጋር በትብብር መስራት፣

3. ከ DHHS እና እና ሌሎች ኤጀንሲዎች እና ድርጅቶች ጋር በመተባበር ለአእምሮ ጤና እና ለዙሪያ ሽፋን አገልግሎቶች ውጫዊ የገንዘብ ድጋፍ ለማግኘት የመለየት፣ ማስተባበርና ማቀንቀን፣ እና

4. አስጊ ባህሪይ ለሚያሳዩ ተማሪዎች፣ እንደየአስፈላጊነቱ፣ በባህርይ እና ጤና ዙሪያ ሽፋን አገልግሎቶችን ለሚያቀርቡ እና ለሚያስተባብሩ ትምህርት ቤቶች ድጋፍ መስጠት።

## III. የዛቻ/ፉከራ/ስጋት ጠባይ ምርመራ-ክትትል ሂደቶች

### A. ዲስትሪክት አቀፍ የባህሪ ስጋት፣ ዛቻ ግምገማ-ምርመራ

1. የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ትምህርት ቤትን መሠረት ያደረገ የአስጊ ባህርይ መርማሪ ቡድኖችን (school-based BTATs) በበላይነት የሚቆጣጠር እና ድጋፍ የሚሰጥ ዲስትሪክት አቀፍ የዛቻና ማስፈራራት መርማሪ ቡድን Behavior Threat Assessment Team (districtwide BTAT) ያቋቁማል/ታቋቁማለች። ዲስትሪክት አቀፍ BTAT የሚመራው በ OSFSE የስነልቦና አገልግሎቶች ዳይረክተር/ተወካይ ሲሆን፣ በስርአት አቀፍ የደህንነት እና የአደጋ ማኔጅመንት ዲፓርትመንት ዋና የደህንነት ኃላፊ/ተወካይ፣ እና OSFSE፣ Office of School Support and Improvement (OSSI)፣ Office of Employee Engagement and Labor Relations (OEELR)፣ Office of Special Education (OSE)፣ Office of the General Counsel (OGC)፣ እና ሌሎች የ MCPS ባልደረቦችን እንደአስፈላጊነቱ ይጨምራል።

2. የዲስትሪክት አቀፍ BTAT ከህግ አስከባሪዎች እና የህዝብ ደህንነት ኤጀንሲዎች፣ የማህበረሰብ የአእምሮ ጤንነት አገልግሎት ሰጪዎች፣ እና DHHS እንደአስፈላጊነቱ ምክክር ያደርጋል።

3. ዲስትሪክት አቀፍ BTAT …

   a) ትምህርት ቤትን መሰረት ያደረጉ የባህሪ ስጋት/ዛቻ ግምገማ/ምርመራ ቡድኖችን ይከታተላል/ይቆጣጠራል፣

   b) በ MCPS፣ DHHS፣ እና የማህበረሰብ የአእምሮ ጤና፣ የህግ አስከባሪዎች፣ እና በሌላ የማህበረሰብ ደህንነት ኤጀንሲዎች መካከል ውጤታማ የሆነ የመረጃ ልውውጥ ሂደትን መጠበቅ፣

   c) በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በጠቅላላ የዛቻ ሥጋት ምርመራ-ክትትል ሂደት ውጤታማ መሆኑን ይገመግማል፣

   d) የዛቻና ማስፈራራት ምርመራ/ክትትል ሂደት ውጤታማ እንዲሆን የታወቁ ምርጥ ተሞክሮዎችን መሠረት በማድረግ በደንቦች እና ሥርዓቶች ላይ እንደአስፈላጊነቱ የለውጦች አስተያየት ማቅረብ፣ እና

   e) በትምህርት ቤት የተመሠረቱ የ BTAT አባሎች በደንብ ስልጠና ያልወሰዱ ከሆነ እና/ወይም ምርመራ ለማድረግ በፍጥነት ለመገኘት የማይችሉ ከሆነና በተማሪዎች እናም በማናቸውም ከ MCPS ያልሆኑ ተማሪዎች (ሠራተኞች፣ ኮንትራክተሮች፣ በጎፈቃደኞች፣ እና ከ MCPS ጋር ግንኙነት የሌላቸው ሰዎችን ጨምሮ) የተደረጉ የሚጠረጠሩ የዛቻና ማስፈራራት ጠባዮችን/አድራጎቶችን ምርመራ ያካሄዳል።

### B. በትምህርት ቤት የሚገኝ BTAT

1. እያንዳንዱ ትምህርት ቤት ርእሰመምህርን/ተወካይ፣ የማስተማር እና የመማር ልምድ ያለው-ያላት የህንጻው አስተዳዳሪ፣ በትምህርት ቤቱ የተመሠረተ የአእምሮ ጤንነት ሠራተኛ (ለምሣሌ፦ የትምህርት ቤት ካውንስለር፣ እና/ወይም የትምህርት ቤት ሳይኮሎጂስት)፣ የትምህርት ቤት ሪሶርስ

ኦፊሰር (SRO) ወይም ሌላ የህግ አስከባሪ ተወካይ፣ እና የትምህርት ቤት ደህንነት ቡድን መሪ እና/ወይም የክለስተር ደህንነት አስተባባሪን የሚያካትት BTAT ይመሠርታል። ሌሎች የሥራ ባልደረቦችን እንደአስፈላጊነቱ ማማከር ይቻላል፣ ነገር ግን ማናቸውም ተማሪዎች ወይም ወላጆች/ሞግዚቶች የትምህርት ቤት BTAT አባል አይሆኑም።

a) ዛቻና ማስፈራራቱን ያደረሰዉ ፣ወይም የደረሰው የልዩ ትምህርት አገልግሎት በሚሰጠው-በሚሰጣት ተማሪ ላይ የተቃጣ ከሆነ፣ የትምህርት ቤት BTAT የልዩ ትምህርት ልምድ ያለው-ያላት እና ለተማሪው(ዋ) የሚሰጠውን ልዩ ትምህርት ፕሮግራም (IEP) ግንዛቤ ያለው-ያላት ሠራተኛ መጨመር አለበት።

b) ዛቻ-ማስፈራራቱ የተፈጸመው፣ ወይም የተቃጣው በ Section 504 plan ተማሪ ላይ ከሆነ፣ የተማሪው(ዋ) ካውንስለር፣ ወይም የ Section 504 አስተባባሪ/ጉዳዩን የሚከታተል-የምትከታተል ማኔጀር፣ መጨመር አለባቸው።

c) ዛቻ-ማስፈራራቱ የተፈጸመው፣ ወይም የተቃጣው የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪ (ELL)/ለሌላ ቋንቋ ተናጋሪዎች የእንግሊዝኛ ትምህርት አገልግሎት (ESOL) ላይ የተቃጣ ከሆነ፣ ትምህርት ቤትን መሠረት ያደረገው BTAT፣ የ ELL/ESOL ልምድ ያለው-ያላት የሥራ ባልደረባ አባል መጨመር አለበት።

2. ርእሰመምህሩ(ሯ)/ተወካይ በትምህርት ቤት የተመሠረተው BTAT መሪ ይሆናል-ትሆናለች፣ እና በትምህርት ቤት የተመሠረተው BTAT አባላት እርስ በርሳቸው፣ ከሌሎች የትምህርት ቤት ባልደረቦች ጋር፣ እና፣ እንደአግባብነቱ፣ በማህበረሰብ ሪሶርስች በትምህርት ቤት የተመሠረተው BTAT ን ዓላማ ለመደገፍ እና የትምህርት ቤትን፣ የተማሪዎቹን፣ እና የሠራተኞቹን ደህንነት ለመደገፍ፣ በትብብር ይሠራሉ። ትምህርት ቤትን መሠረት ያደረገ የ BTAT መሪ እንደአስፈላጊነቱ እና እንደአግባብነቱ ከዲስትሪክት አቀፍ BTAT ጋር መማከር ይኖርበ(ባ)ታል።

3. ትምህርት ቤትን መሠረት ያደረገ BTAT አባላት በሙሉ ስለ...ስልጠና ይወስዳሉ–

a) ለጉዳዮች ደረጃ መስጠት እና ጉዳዩን ማስተዳደር፣ የሚያካትተዉም –

1) ጣልቃ-ገብነትን መወሰን እና መዘገብ/ዶኩመንት ማድረግ፣

2) ወደ ውጫዊ ሪሶርሶች ማስተላለፍ፣

3) ለሚመለከታቸው ተማሪዎች እና ሠራተኞች በሙሉ ድጋፍ-እርዳታ መስጠት፣ እና/ወይም

4) ማንኛውንም የትምህርት ቤት ከባቢያዊ ወይም የአየር ንብረት ሁኔታዎችን መምራት/መቆጣጠር፣

b) ለዘር እና ለጎሰኝነት ልዩነቶች ልዩ ትኩረት በመስጠት ግልጽ አድሎን በመረዳት የአካል ጉዳተኝነት እና ብዝሃነት ግንዛቤን ማዳበር፤

c) አስጊ ሁኔታዎችን በሚመለከት ከዚህ በላይ በ"Section II.A.2" ላይ በተገለጸው መሠረት አስፈሪና አስጊ ባህርይን "Pathway to Violence" በመጠቀም መገምገም፤

d) የተማሪን ገመና እና ይፋ ያለማድረግ መስፈርቶችን፣ የቤተሰብ ትምህርታዊ መብቶች እና ገመና ደንብን/Family Educational Rights and Privacy Act (FERPA)፣ እና SRO Memorandum of Understanding (SRO MOU) የመግባቢያ ሠነድን ጨምሮ [1]እና ተዛማጅነት ያላቸው የሪፖርት አቀራረብ ፕሮቶኮሎችን አጥብቆ መከተል፣ እና

e) ስትራተጂዎችን እና መመሪያዎችን መገንዘብ አስቸጋሪ ባህርይን ስለመገምገም ሞዴል ፖሊሲ - Model Policy for Behavior Threat Assessment በሜሪላንድ የትምህርት ቤት ደህንነት ማእከል - (Maryland Center for School Safety) ንኡስ ካቢኔት አማካይነት እንደተገለጸው።

4. የትምህርት ቤትን፣ የተማሪዎችን፣ ወይም የሠራተኞችን ደህንነት ስጋት ላይ የሚጥሉ ነገሮች ሲከሰቱ፣ የማያስፈልግ ካልሆነ በስተቀር፣ የ BTAT አባሎች በሙሉ የዛቻና ማስፈራራት ባህርይ በሚያሳዩ ግለሰቦች ባህርይ ምርመራ እና ጣልቃ ገብነት ስራ ላይ መሣተፍ ይኖርባቸዋል።

5. በትምህርት ቤት የተመሠረተ BTAT –

a) ሊሆኑ የሚችሉ የማስፈራሪያ ባህርዮችን ስለመገንዘብ/ለይቶ ስለማወቅ እና አዘጋጅቶ በማቅረብ/presentations ላይ የተመሠረተ፣ ዘርዘር ብሎ የተቀናበረ ጠቃሚ መረጃ፣ እና ከትምህርት ቤት BTAT ምክር/ኮንሰልቴሽን እንደሚገኝ በማረጋገጥ የማስፈራሪያ ባህርዮችን ሪፖርት የማድረግ ሂደት ለተማሪዎች እና ለሠራተኞች መመሪያ መስጠት፣ እና

b) በትምትህርት ቤት ሠራተኞች፣ ወይም ተማሪዎች ላይ፣ ዛቻ እና ማስፈራራት በሚያደርጉ ግለሰቦች ባህርይ ላይ ለምርመራ እና ጣልቃገብነት፣ እንደአስፈላጊነቱም ወደ ማህበረሰብ አገልግሎት ድርጅቶች ወይም የጤና እንክብካቤ ለሚሰጡ ተቋማት ለምርመራ ወይም ለህክምና ለማስተላለፍ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ፖሊሲዎችን እና ደንቦችን በውጤታማነት ተግባራዊ ማድረግ፣

6. እያንዳንዱ በትምህርት ቤት የተመሰረተ BTAT ቢያንስ በየወሩ እየተሰበሰቡ ያልተጠናቀቁ ወይም እየተንቀሳቀሱ ያሉ ጉዳዮችን እና ከዝቅተኛ እስከ ምንም ዛቻና ማስፈራራት የማይባሉ ሁነቶችን ሪፖርቶች ይገመግማሉ። ትምህርት ቤትን መሠረት ያደረገው BTAT ከዲሲትሪክት አቀፍ BTAT የተሰጠውን የሪፖርት አቀራረብ ሂደት በመከተል ያልተፈጸሙ ጉዳዮችን ለዲሲትሪክት አቀፍ BTAT ያሳውቃል።

7. የትምህርት ቤትን፣ የተማሪዎቹን እና የሠራተኞቹን ደህንነት ለመደገፍ ትምህርትን ቤት መሠረት ያደረገ BTAT አባሎች በንቃት፣ በህጋዊነት፣ እና በመልካም ስነምግባር እርስበርሳቸው፣ ከትምህርት ቤት አስተዳዳሪዎች፣ እና ከሌሎች የተለየ መረጃ ማወቅ ከሚፈልጉ የትምህርት ቤት ባልደረቦች ጋር ይገናኛሉ።

C. አስጊ ሁኔታዎችን በመለየት ሪፖርት ማድረግ

---

[1] ሙሉ አርእስት፡- በ MOU ህግ አስከባሪ የተሳተፈበት ክስተቶች ሪፖርት አቀራረብ ፕሮቶኮሎች በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) እና በሞንትጎመሪ ካውንቲ የፖሊስ ዲፓርትመንት (Montgomery County Department of Police) እና በሞንትጎመሪ ካውንቲ የሸሪፍ ጽ/ቤት (Montgomery County Sheriff's Office) እና በሪክቪል ከተማ የፖሊስ ዲፓርትመንት (Rockville City Police Department) እና በጌትስበርግ ከተማ የፖሊስ ዲፓርትመንት (Gaithersburg City Police Department) እና በታኮማ ፓርክ የፖሊስ ዲፓርትመንት (Takoma Park Police Department) እና በሞንትጎመሪ ካውንቲ የስቴት ዓቃቤ ህግ ጽ/ቤት (Montgomery County State's Attorney's Office): ሶሮ ፕሮግራም (SRO Program) እና በትምህርት ቤት ለሚፈጠሩ ክስተቶች ሌላ የህግ ማስከበር ምላሾች (SRO MOU)

1. የ MCPS ሠራተኛ አይቀሬ የሆኑ ህይወትን የሚያሰጋ ወይም በደህንነት ላይ የተቃጣ ዛቻና ማስፈራራትን በፍጥነት ሪፖርት ለማድረግ በዚህ ደንብ ላይ ምንም የተከለከለ ነገር የለም።

2. የ MCPS ተማሪዎች፣ ሠራተኞች፣ በጎፈቃደኞች፣ እና ኮንትራክተሮች ማንኛውንም ዛቻና ማስፈራሪያ ለርእሰመምህር/ተወካይ፣ ወይም ለማናቸውም የ MCPS የሥራ ባልደረባ፣ በፍጥነት ሪፖርት ማድረግ አለባቸው። እንዲህ ዓይነት ሪፖርት የሚያገኙ ሠራተኞች ወዲያውኑ መረጃውን ለርእሰመምህር/ተወካይ ማስተላለፍ አለባቸው።

3. ርእሰመምህሩ(ሯ) የዛቻና ማስፈራራቱ ሪፖርት እንደደረሰው/እንደደረሳት፣ በእርግጠኝነት ዛቻው መኖር/አለመኖሩን በፍጥነት ማረጋገጥ ያስፈልጋል። ይህ ማረጋገጫ ከተደረሰ በኋላ፣ ርእሰመምህሩ(ሯ)/ተወካይ የቦርድ ፖሊሲዎችን፣ የ MCPS ደንቦች እና ህጎችን፣ እና የ SRO MOU መመሪያዎች በሚደነግጉት መሠረት ለህግ አስከባሪዎች እና/ወይም ለማህበረሰብ ደህንነት ኤጀንሲዎች ያሳውቃሉ።

4. ከዛቻና ማስፈራራት የምርመራ እንቅስቃሴ ባለፈ፣ ለ OSSI ማሳወቅ እና ለህግ አስከባሪዎች መምራት መደረግ ያለባቸው በቦርድ ፖሊሲዎች፣ የ MCPS ደንቦች እና ህጎች፣ በተጨማሪም –

    a) የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ደንብ - MCPS Regulation EKA-RA፣ የአስቸኳይ እና ቀውስ ሁኔታ ቅድመ ዝግጅት - Emergency and Disaster Preparedness፣

    b) የቦርድ ፖሊሲ JHC - Board Policy JHC, የልጅ መጎሳቆል እና ቸልተኝነት - Child Abuse and Neglect፣ እና የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ደንብ JHC-RA/MCPS Regulation JHC-RA የልጅ ማጎሣቆልን ሪፖርት ስለማድረግ እና ምርመራ - Reporting and Investigating Child Abuse and Neglect፣

    c) የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ደንብ COB-RA - MCPS Regulation COB-RA፣ ክስተትን ሪፖርት ስለማድረግ - Incident Reporting፣

    d) የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የተማሪ ስነምግባር ኮድ - Student Code of Conduct in Montgomery County Public Schools፣ እና

    e) የ SRO MOU።

5. ለወላጅ/ሞግዚት ማሳወቂያ

    a) ከህግ አስከባሪዎች ጋር በመምከር፣ ርእሰመምህሩ(ሯ)/ተወካይ ስለዛቻውና ማስፈራራቱ ሁኔታ ለማሳወቅ እና/ወይም ሪፖርት ስለተደረገው ሁኔታ ለመግለጽ፣ ምርመራው ልጅን የማጎሣቆል ወይም ቸልተኝነት ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር ጉዳዩ የሚመለከታቸውን ተማሪ(ዎች) ወላጆችን/ሞግዚቶችን ለማግኘት ጥረት ያደርጋል-ታደርጋለች።

    b) ርእሰመምህር/ተወካይ ወላጆች/ሞግዚቶች የበለጠ መረጃ ለማግኘት ከፈለጉ ማግኘት የሚገባቸውን የህግ አስከባሪ ኤጀንሲ ይገልጹላቸዋል።

    c) ከልጅ ማጎሣቆል እና ቸልተኝነት ጋር የተያያዙ ጥርጣሬዎችን በሚመለከት ለወላጅ/ሞግዚት የማሳወቅ አሰራር የቦርድ ፖሊሲ - Board Policy JHC፣ ድንጋጌን

መከተል አለበት፣ ልጅን ማጎሳቆል እና ቸልተኝነት/Child Abuse and Neglect እና የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ደንብ/MCPS Regulation JHC-RA የህፃናት ጉስቁልና እና ቸልተኝነት ምርመራ/Reporting and Investigating Child Abuse and Neglect።

D. ስለደረሰው ጉዳት የመጀመሪያ ምርመራ

1. ማናቸውም ዛቻ ሪፖርት በሚደረግ ጊዜ፣ እና "section III.C" እንደተብራራው ስለተከሰተው የዛቻ ሁኔታ ተገቢውን የሪፖርት አቀራረብ ፕሮቶኮሎችን በመከተል የዛቻው ሁኔታ ወደ ትምህርት ቤት BTAT መሪ መተላለፍ አለበት።

2. የሚያሰጋ አይነት ማስፈራሪያ ካልኖረ፣ ወይም የማስፈራራቱ ስጋት ቁጥጥር ስር ከዋለ፣ የትምህርት ቤት BTAT ቡድን መሪ ትምህርት ቤትን መሠረት ካደረገው የ BTAT ቡድን አባላት ውስጥ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ አባላትን በመለየት የዛችና ማስፈራራት መርማሪ ቡድን አባላት በሙሉ መሣተፍ ይኖርባቸው እንደሆነ ለመወሰን የምርመራ ደረጃ ማሳወቂያ ያበረታታል/ታበረታታለች/እንዲከወን ያደርጋል/ታደርጋለች። ከሁለቱ የቡድን አባላት ቢያንስ አንዳቸው የትምህርት ቤት የአእምሮ ጤና ሥራ ባልደረባ መሆን አለበ(ባ)ት።

3. እንደአስፈላጊነቱ እና እንደአግባቡ ጉዳትን የመመርመር ሂደት የሚያካትተው –

a) የዛቻና ማስፈራሪያ ባህርይ ወይም ግንኙነትን በሚመለከት የመጀመሪያ ሪፖርት እና ማናቸውንም ተጨማሪ መረጃዎች በመገምገም፣

b) ጉዳዩ የሚመለከተው-የሚመለከታት/የሚመለከታቸው ግለሰብ(ግለሰቦች) የቅድሚያ ታሪክ ወይም ጣልቃ ገብነት በትምህርት ቤት ወይም ሌላ ሪኮርዶች ካሉ ምርመራ ማድረግ፣

c) ስለማስፈራሪያው ተጨማሪ ጠቃሚ መረጃ ለማግኘት ከ SRO ወይም የህግ አስከባሪዎች ጋር ምክክር ማድረግ፣

d) ክስተቱን ሪፖርት ካደረገ(ች)ው (ካደረጉት) ሰዎች፣ ጉዳዩን ከሚያውቀው/ከምታውቀው- ከሚያውቁት፣ ወይም ወይም ማስፈራራት ከተደረገበ(ባ)ት፣ ሌሎች ዛቻና ማስፈራራቱን ካወቁትና ምስክር ከሚሆኑ ሰዎች፣ እና ምክንያታዊ የሚሆን ከሆነ፣ በማስፈራራቱና በዛቻ ምግባር ወይም በግንኙነቱ ተሳትፈዋል ተብለው ከሚጠረጠሩት ግለሰቦች ወቅታዊ እና ዝርዝር ቃለመጠይቆችን ማካሄድ፣ ቃለመጠይቅ የማድረጉ ዓላማ የዛቻና ማስፈራራቱን ሁኔታ ለመገምገምና፣ የግለሰቡ(ቧ) ማስፈራሪያ እና አዝማሚያ ትርጉሙን ለማገናዘብ፣ እና፣

e) እንደማስፈራሪያው ሁኔታ አጣዳፊነት እና አስፈላጊነት በተቻለ መጠን በፍጥነት ውሳኔ ለመስጠት እና –

(1) ያሉት ሪሶርሶች እና ዘይቤዎች መጠን ያለውን ስጋት ለማቃለል በቂ የመሆን፣ ወይም

(2) ወይም BTAT በሙሉ ሁኔታውን ማኔጅ ለማድረግ ይበልጥ ቅኝት ማድረግ ካለባቸው።

4. የትምህርት ቤት BTAT መሪ እንደአስፈላጊነቱ የጣልቃ ገብነት ድጋፍ በማዘጋጀት ተግባራዊ ያደርጋል-ታደርጋለች፣ ይህም የሚያካትተው –

   a) ለአጠቃላይ ትምህርት እና/ወይም የልዩ ትምህርት ከሪኩለም ተማሪ ተደራሽነትን ለመደገፍ እና ተማሪው(ዋ) ለልዩ ትምህርት አገልግሎት ብቁነት መገምገም ያስፈልግ እንደሆነ ለመወሰን የማህበራዊ-ስሜታዊ/ስነምግባር ጣልቃ ገብነቶችን አሠራር በማዘጋጀት ተግባራዊ ለማድረግ የትምህርት ማኔጅመንት ቡድን/Educational Management Team (EMT) መሰብሰብ፣ እና

   b) የተማሪው(ዋ)ን የ "Section 504 ወይም IEP" ቡድን ለስብሰባ በመጥራት እቅዱን መገምገም እና ሒደቱ እንዲጀመር ማድረግ የ functional behavioral assessment FBA) እና ውሳኔ መጻፍ ስለ ባህርይ ጣልቃ ገብነት እቅድ (BIP)፣ የዋስትና ሠነድ/ማዘዣ ከተሰጠ እና ተማሪው(ዋ) ቀደም ሲል የሌለው/የሌላት ከሆነ።

5. የስጋት መንስኤ የሆነ(ች)ው ሰው የ MCPS የሥራ ባልደረባ ከሆነ(ች)፣ ርእሰመምህር/ተወካይ በፍጥነት ወደ OEELR ማሳወቅ፣እና በቅድሚያ መርማሪ ቡድን የተሰበሰበውን እና የተገመገመዉን ዶኩመንት/ሰነዶች በሙሉ ለዲስትሪክት አቀፍ BTAT ማቅረብ።

6. የስጋት መንስኤ የሆነው-የሆነችው ሰው የ MCPS ተማሪ ካልሆነ(ች)፣ ክስተቱ በፍጥነት ወደ ዲስትሪክት አቀፍ BTAT መተላለፍ ይኖርበታል።

E. ከዝቅተኛ እስከ ምንም የሚያሰጋ ነገር የለም/Low to No Threat Risk

ምንም የሚያሰጋ ማስፈራራት እንደሌለ፣ ወይም ጠቡ/ረብሻዉ የሚያስከትለው የስጋት ደረጃ ወይም ጉዳት ዝቅተኛ በመሆኑኑ ምንም ቀጣይ ምርመራ፣ ጣልቃገብ ተግባር፣ ወይም ቁጥጥር ጠቡን/ረብሻዉን ለመከላከል እንደማያስፈልግ፣ ትኩረት/ቅድሚያ ሰጪው ቡድን ካረጋገጠ፣ እንደአግባብነቱ እና እንደአስፈላጊነቱ የሚከተለው መደረግ አለበት፡-

1. ውሳኔው በተሰጠ 24 ሠዓት ውስጥ፣ የትምህርት ቤት BTAT መሪ ክስተቱን እና የቅድሚያ/ትኩረት ቡድኑን ግምገማ በበቂ ሁኔታ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የክስተት ማኔጅመንት ሲስተም/MCPS Incident Management System ላይ በትክክል መመዝገቡን ማረጋገጥ አለበ(ባ)ት።

2. ክስተቱ ጉልበት ተጠቅሞ ማጥቃት፣ መተናኮስ፣ ማስፈራራት ተብለው የሚገመቱ ባህርዮች ያሉበት ከሆነ፣ የትምህርት ቤቱ BTAT መሪ የ MCPS Form 230-35 Bullying, Harassment, or Intimidation Reporting Form መሞላቱን በማረጋገጥ፣ ርእሰመምህር/ተወካይ አማካይነት ምርመራ እንዲካሄድ MCPS Form 230-36 Bullying, Harassment, or Intimidation Incident School Investigation Form ይሞላል/ትሞላለች።

3. በራስ ላይ ጉዳት የማድረስ ወይም ራስን የመግደል ስጋት ከተፈጠረ፣ የትምህርት ቤት BTAT መሪ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ቅጽ-"MCPS Form 335-54" ራስን የመግደል ስጋት ሪፖርት የሚደረግበት ቅጽ-Suicide Risk Reporting Form መሞላቱን ማረጋገጥ እና አግባብነት ባለው የትምህርት ቤት ሠራተኛ አማካይነት ራስን የመግደል ስጋት ምርመራ መደረጉን ጭምር በማረጋገጥ፣ ተገቢ ከሆነም ተማሪው(ዋ)ን ወደ ሞንትጎመሪ ካውንቲ የቀውስ ማእከል እና/ወይም ወደ ግል አገልግሎት ሰጪ (ፕሮቫይደር) መምራት ያስፈልጋል። በሌሎች ላይ ጉዳት ለማድረስ በሚያስፈራራ/በሚዝት-በምታስፈራራ/በምትዝት ተማሪ ላይ BTAT ምርመራ በሚያደርግበት

ወቅት፣ ትምህርት ቤትን መሠረት ያደረገው BTAT ራስን ስለመጉዳት እና ራስን ስለማጥፋት ሃሳብ ጭምር መመርመር ይኖርበታል።

4. የተከሰተው ሁኔታ የልጅ ማጎሣቆል ወይም ቸልተኝነት ተደርጎ የሚቆጠር ከሆነ፣ ስለ ልጅ መጎሳቆል እና ቸልተኝነት ሪፖርት የሚደረግበት የቦርድ ፖሊሲ/Board Policy JHC ሂደትን፣ Child Abuse and Neglect፣ እና MCPS Regulation JHC-RA፣ Reporting and Investigating Child Abuse and Neglect መከተል ያስፈልጋል።

F. ከመካከለኛ እስከ ከፍተኛ ስጋት

1. ቅድሚያ ደራሽ ቡድኑ ማረጋገጥ/መወሰን ካልቻለ፣ አስተማማኝ በሆነ ደረጃ፣ ተለይቶ የሚታወቅ ስጋት አለመኖሩን፣ ወይም መጠነኛ የሆነ ስጋት ከሆነ፣ የደህንነት ስጋትን ለማጣራት እና ሁከት/ብጥብጥ ለመከላከል እና ስጋትን የመቀነስ ስትራቴጂ ለማዘጋጀት በትምህርት ቤት BTAT በሙሉ አኳኋኑን እና መጠኑን ለማወቅ የበለጠ ጥልቀት ያለው የዛቻና ማስፈራራት ባህርይ ምርመራ ያካሄዳል። እነዚህ ፕሮቶኮሎች ተግባራዊ የሚሆኑት አስጊውን ሁኔታ መቆጣጠር ከተቻለ በኋላ ነው።

2. የትምህርት ቤት BTAT መሪ ከዋና የደህንነት ኦፊሰር ጋር እና የስነልቦና አገልግሎት ዳይሬክተር ወይም የእነርሱ ተወካይ-ተወካዮች በመነጋገር ተማሪው(ዋ) ሁከት/ብጥብጥ ወይም የአካል ጉዳት የማድረስ ስጋት የደቀነ(ች) መሆኑን እና የተፈጠረውን ክስተት ለመገምገም ሂደት ትምህርት ቤትን መሠረት ያደረገ BTAT የዋና ጽ/ቤትን ድጋፍ የሚሻ መሆኑን ለትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት/ተወካይ ሪፖርት ለማድረግ የመጀመሪያ ደረጃ ውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል። ከዋና የደህንነት ኦፊሰር እና የስነልቦና አገልግሎት ዳይሬክተር ወይም የእነርሱ ተወካይ ጋር የተደረገውን ውይይት በትምህርት ቤት የተመሠረተው BTAT መሪ ለዚህ ተግባር የተዘጋጀውን የ MCPS ቅጽ በመሙላት በሠነድነት ይይዛል/ትይዛለች።

3. የትምህርት ቤት BTAT መሪ የ BTAT ግምገማ በሚካሄድበት ጊዜ ለተማሪው(ዋ) ተገቢ የሆኑ ጥበቃዎች እንዲኖሩ ያደርጋል/ታደርጋለች። የ MCPS ሠራተኞች ያልሆኑ ትምህርት ቤትን–መሠረት ያደረገ BTAT አባላት በመጀመሪያው የ BTAT ስብሰባ ወቅት የመተማመኛ እና ሚስጥር የመጠበቅ ሠነድ መፈረም ይኖርባቸዋል። ከዚህ በታች የተገለጹት በተጨማሪ ይፋ የማይደረጉ ናቸው።

4. የዛቻና ማስፈራራት ባህርይ ምርመራ በዚህ የማይወሰን ባይሆንም የሚከተሉትን ያካትታል፦

a) ሪኮርዶችን መመልከት

(1) የማስፈራራት ዛቻ መርማሪ ቡድን አባል የሆነ(ች) የህግ አስከባሪ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ የወንጀል ሪኮርድ ታሪክ ያላቸውን መረጃዎች ለተጨማሪ ምርመራ ጠይቆ የማግኘት እና የማስፈራራት ሁኔታዎችን ለመመርመር ይችላል/ትችላለች።

(2) በትምህርት ቤት የተመሠረተው BTAT ሥራዎቹን ለማከናወን እንዲችል፣ የተማሪው(ዋ)ን የትምህርት እና የጤና ሪኮርዶችን ማግኘት ያስፈልግ ይሆናል።

(3) የትምህርት ቤት BTAT ግምገማ የሚደግፍ የተማሪው(ዋ)ን የማህበራዊ ሚድያ አካውንቶች፣ የኢንተርኔት እንቅስቃሴ፣ የአገልግሎት ጥሪዎችን፣ እና

ሌሎች መረጃዎች ወይም ዳታ ለማወቅ ተጨማሪ መረጃ የመሰብሰብ ቴክኒክ መጠቀም ሊያስፈልግ ይችላል።

b) ከትምህርት ቤት የ BTAT የህግ አስከባሪ ተወካይ ጋር በመነጋገር፣ እና በ SRO MOU ድንጋጌ መሠረት፣ የትምህርት ቤት የ BTAT የማስፈራራት ዛቻውን ሪፖርት ካደረጉት፣ ዛቻ ከተደረገባቸው ወይም የጥቃቱ ዒላማ ከተደረጉ እና ሌሎች ምስክር ሆነው የማስፈራራቱን ሁኔታ ከሚያውቁ እና አሳማኝ ምክንያት ካለው በማስፈራራት ባህርይ ወይም ግንኙነት ተሳትፈዋል ተብለው ከሚጠረጠሩት ሰዎች ጋር (እንደአስፈላጊነቱ) ወቅታዊ እና ዝርዝር ቃለመጠይቆችን ማከናወን ይኖርበታል።

c) የቃለመጠይቆቹ ዓላማ የግለሰቡ(ቧ)ን ዛቻ-ማስፈራራት አገባብ፣ አጠቃላይ ሁኔታ ለመገምገም እና የዛቻው/የማስፈራራቱ ትርጉም እና የግለሰቡ(ቧ)ን አዝማሚያ ለመወሰን ነው።

d) ከዚህ በላይ Section III.E.4 ላይ እንደተገለጸው ተገቢ የሆነ ጣልቃገብነት እና ድጋፎች ተግባራዊ ይደረጋሉ።

5. ትምህርት ቤትን መሠረት ያደረገ BTAT ከዚህ በላይ በ "Section II.A.2" በተገለጸው መሠረት በምርመራ የተገኙት ማረጋገጫዎች ጉዳዩ የሚመለከተው-የሚመለከታት ተማሪ የፈጸመ(ች)ው ጥሰት ወዴት እንደሚያመራ "Pathway to Violence" ለመወሰን የሚያሰጋ ባህርይን በመተንተን ይመረምራል።

a) በተረጋገጠ በ 24 ሠዓት ጊዜ ውስጥ፣ በትምህርት ቤት የተቋቋመው BTAT መሪ የተከሰተው ሁኔታ በ "MCPS Incident Management System" ላይ በትክክል ዶኩመንትድ መሆኑን/የተመዘገበ መሆኑን ያረጋግጣል/ታረጋግጣለች።

b) ከህግ አስከባሪ ጋር በመወያየት፣ ርእሰመምህር/ተወካይ SRO MOU መመሪያ መሠረት ጉዳዩ ለሚመለከተው-ለሚመለከታት ተማሪ ወላጆች/ሞግዚቶች እና በምርመራው ውጤት መሠረት ዒላማ ተደርጓል-ተደርጋለች ተብሎ ለተጠረጠረ(ች) ግለሰብ፣ በተቻለ ፍጥነት ማሳወቅ ይኖርበ(ባ)ታል።

G. ጣልቃገብነት፣ መቆጣጠር፣ እና ዛቻ-ፍርሃትን መፍትሔ ማስገኘት

እንደማናቸውም የአስጊ ስነምግባር ምርመራዎች፣ በትምህርት ቤት የተመሠረተ BTAT ያሉትን ሪሶርሶች የህግ አስከባሪዎችን እና ሌሎች የማህበረሰብ ደህንነት ኤጀንሲዎችን እና የማህበረሰብ እርዳታ ድርጅቶችን ጨምሮ፣ ስለሚመለከተው ተማሪ እና ሌሎችም ተጋላጭነት ላላቸው እንደአስፈላጊነቱ የኬዝ ማኔጅመንት እቅድ ማዘጋጀት።

1. የኬዝ ማኔጅመንቱ እቅድ ደህንነትን እና ስትራቴጂን ንድፍ ያወጣል፣ ኃላፊነቱ የሚመለከታቸው ሰዎች፣ እና የአተገባበር ጊዜ ማዕቀፍ፣ እና የሚሰጡ ድጋፎችን ውጤታማነት ለመቆጣጠር አመቺ የሆነ ስርአት ይገልጻል/ይነድፋል። የእንደዚህ አይነት ድጋፍ ምሳሌዎች የሚያካትቱት፡- ነገር ግን በዚህ አይወሰንም፣ መርሃግብሮችን እንደገና መቀያየር፣ እገዳዎችን/ገደቦችን ማብጀት፣ ግላዊ ካውንስሊንግን ወደ ማህበረሰብ ሪሶርስ ማስተላለፍ፣ የህክምና አገልግሎቶች፣ ወይም አካደሚያዊ ድጋፎች፣ እና/ወይም ትምህርት ቤትን መሠረት ያደረገ የሠላምና ደህንነት እቅድ ማዳበር።

2. የተዋጣለት የኬዝ ማኔጅመንት እንደየአስፈላጊነቱ እና እንደጠቀሜታው መጠን፣ ጣልቃገብነቶችን ያቀናጃል፣ በዚህ የተወሰነ ባይሆንም የሚያካትታቸዉ –

a) እየተባባሰ እንዳይሄድ፣ ከቁጥጥር ስር ማዋል፣ ወይም የሁከት-ብጥብጥ እርምጃ የሚወስደውን-የምትወስደውን የጉዳዩን ባለቤት መቆጣጠር፣

b) ዒላማ የተቃጣበ(ባ)ትን ተጋላጭነት እንዲቀነስ ማድረግ፣

c) አካላዊ እና/ወይም ባህላዊ አካባቢን እና ሲስተም በማሻሻል የመባባስ/የመጨመር ሁኔታን ማጨንገፍ፣

d) ያልተጠበቁ፣ ድንገተኛ ክስተቶችን ተፃራሪ-የሚጎዳ አጸፋ ምላሾችን ለመቀነስ/ ለማቅለል/ለማስታገስ መዘጋጀት። ተማሪው(ዋ) ሁከት ለመፍጠር እንደሚችል-እንደምትችል ከተረጋገጠ፣ የትምህርት ቤት BTAT አስጊ ሁኔታን ለመቀነስ/ለመግታት የሚያስችል ግላዊ የጣልቃ ገብነት እቅድ በማዘጋጀት ተግባራዊ ማድረግ፣ እና

e) እንደአስፈላጊነቱ ስለ ተጨማሪ የማህበረሰብ ኤጀንሲ ጣልቃገብነት ለህግ አስከባሪ ማሳወቅ።

## IV. የተማሪ ሪኮርዶች

A. ማንኛውም የ BTAT አባል የዛቻና ማስፈራራት ምርመራ በማድረግ የተገኘ ማንኛውንም የወንጀል ታሪክ ሪኮርድ መረጃ እንደገና ይፋ ማድረግ ወይም ካልሆነም ለ BTAT ሥራውን ለማስፈጸም የተሰጠን ግላዊ ሪኮርድ ከዓላማው ውጪ ለሆነ ነገር መጠቀም አይኖርበትም።

B. BTAT ሥራውን ለማከናወን ያገኛቸውን ግላዊ የወንጀል ታሪክ ሪኮርድ መያዝ የለበትም ወይም አባሎቹ ቅጂ ማድረግ አይኖርባቸውም።

C. የወንጀል ታሪክ መረጃ በተማሪው(ዋ) የትምህርት ማህደር ጋር አይቀመጥም ወይም FERPA, 34 CFR §99.3. ላይ እንደተገለጸው ከተማሪ የትምህርት ሪኮርድ ጋር አይያዝም።

D. የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የስራ ባልደረቦች ያልሆኑ የ BTAT አባሎች የተማሪን ሪኮርዶች ይፋ የማያደርጉ እና በሚስጥር የሚጠብቁ መሆናቸውን ማረጋገጫ መፈረም ይኖርባቸዋል።

**ተዛማጅ ምንጮች፡-** Family Educational Rights and Privacy Act (FERPA)፣ 20 U.S.C. §1232g፣ 34 CFR Part 99፣ Protection of Pupil Rights Amendment (PPRA)፣ 20 U.S.C. §1232h፣ 34 CFR Part 98፣ (2000 and Supp. IV 2004)፣ Maryland Student Data Privacy Act of 2015፣ Annotated Code of Maryland, Education Article, §4- 131፣ Maryland Safe to Learn Act, Md. Code Ann., Educ. §7-1507፣ MSDE Model Policy for Behavior Threat Assessment

**የዚህ ደምብ ታሪክ፦** አዲስ ደምብ፣ ኦገስት 26/2019።

**ማስታወሻ፦** አባሪ የተደረገ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ደምብ COA-RA - "MCPS regulation indexed as COA-RA" ስለ ትምህርት ቤት ጉብኚዎች ጁላይ 1/2008 በተሻረው የሞንትጎመሪ ካውንቲ ደንብ ABA-RB - MCPS Regulation ABA-RB ተካቷል።